EPA
የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY

በኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

የቢሾፍቱ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ተሞክሮ



2017 ዓ.ም አዲስ አበባ

ማውጫ

መግቢያ 1

1. ክፍል አንድ - የስራው ሁኔታ 2

1.1. ዓላማ 2

1.1.1. ዋና ዓላማ 2

1.1.2. ዝርዝር ዓላማዎች 2

1.2. አስፈላጊነት 2

1.3. ወሰን 2

1.4. የመረጃ አሰባሰብ ስልት 2

2. ክፍል ሁለት 3

2.1. ቢሾፍቱ ከተማ 3

2.2. በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ከመጀመሩ በፊት አካባቢው የነበረበት ሁኔታ 4

2.3. የቆሻሻ አያያዝና አወጋድ ችግሮችን ለመፍታት የተከናወኑ የግንዛቤ ሥራዎች 4

2.3.1. በግንዛቤ የተገኘ ለውጥ 4

2.4. የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 4

2.5. የተሟሉ ግብዓቶችና የቴክኖሎጂ ውጤቶች 5

2.6. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ ማሕበራት 5

2.7. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ 6

2.7.1. የክፍያ ሁኔታ 6

2.7.2. ደረቅ ቆሻሻን በየአይነቱ የመለየት ስራ 6

2.7.3. የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ መቀባበያ ቦታዎች 7

2.8. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) 7

2.9. ቴክኖሎጂ አጠቃቀም 9

2.10. የሥራ ዕድል ፈጠራ 9

2.11. ቅንጅታዊ ስራ 9

2.12. በተከናወኑ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ እንዲሁም በውበትና መናፈሻ ስራ ውስጥ በመልካም ተሞክሮነት የሚወሰዱ 9

2.12.1. ሞዴል መንደር 9

2.12.1.1. ዝቋላ መንደር 10

2.12.1.2. አዳ መንደር 11
2.12.1.3. ሰላም መንደር 12
2.13. ቀልዝ (ኮምፖስት) የሚያዘጋጁ ማህበራትና ዝግጅት 13
2.14. የኮሪደር ልማት ስራ 14
2.15. ሀይቆች 16
2.16. ችግኝ ጣቢያ 16
3. ክፍል ሦስት፡- 17
ማጠቃለያ 17

መግቢያ

ዜጎች ንጹህ እና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው የኢትዮጵያ ህገመንግስት አንቀጽ 44 ያስገነዝባል። በመሆኑም መንግስት የአካባቢ ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚረዱ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል ።

በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ህብረተሰብን በማሳተፍ የሚከናወኑ በርካታ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ይገኛሉ። እነዚህ ተግባራት ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሚናቸው የጎላ ነው።

የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድና አያያዝ ጉድለት የአብዛኞቹ የሀገራችን ከተሞች ችግር እንደሆነ ይታወቃል። ለዚህም መነሻ ምክንያቶች ከሆኑት መካካል ከፍተኛ የነዋሪው ህዝብ ቁጥር መጨመርና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የህዝብ ፍልሰት ሰፊውን ቦታ ይይዛል። በተጨማሪም በቆሻሻ አወጋገድ፣ አስተዳደርና አፈፃፀም እንዲሁም አጠቃቀም ዙሪያ በነዋሪዎች ዘንድ የሚታየው የግንዛቤ ጉድለት ይታያል።

በመሆኑም ጉድለቶቹን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ባለመዘርጋቱ ከተሞችን ጽዱና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት እያደናቀፈ ይገኛል። በየከተሞቹ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በየቦታው የሚጣለው ቆሻሻ ነዋሪዎችን ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እያጋለጠ ስለሆነ ለጤናማ ህይወት አስቸጋሪ በመሆኑ ዋነኛ የቅሬታ ምንጭ እየሆነ ይገኛል።

የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በከተሞች የሚከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አሰራር ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ ቀጣይ ለሚደረጉ የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥራዎች በግብዓትነት ለመጠቀም እና የተሸለ ተሞክሮ ለማስፋት እየሰራ ይገኛል።

በዚሁ መሠረት በኦሮሚያ ክልል በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድና አያያዝ ስርዓትን በማሻሻል ቆሻሻውን ከቤት ለቤት ልየታ ጀምሮ እስከ ቆሻሻ ማስወገጃያ ያለውን ሂደት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የተከናወኑ ተግባራት ለሌሎች አስተማሪ ሆነው የሚታዩ ናቸው። እንዲሁም የኮሪደር ልማት ሥራዎች እና አረንጓዴ ቦታዎች የእንክብካቤ ሥራዎች የሚበረታቱ ናቸው። በመሆኑም በከተማው ውስጥ የተከናወኑ ለመልካም ተሞክሮ የሚሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ይህ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

ክፍል አንድ - የስራው ሁኔታ

1.1. ዓላማ

1.1.1. ዋና ዓላማ

በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የተከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንዲሁም የኮሪደር ልማት ስራዎችን በመልካም ተሞክሮነት ቀምሮ በተለያዩ ስልቶች ሌሎች እንዲማሩበት ማድረግ።

1.1.2. ዝርዝር ዓላማዎች

የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በማዘመን አካባቢን ጽዱና አረንጓዴ ለማድረግ ዜጎች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ

ቆሻሻ ሀብት መሆኑን በመረዳት ዜጎች በዚህ ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማበረታታትና ለማስፋት፣

1.2. አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ህገመንግስት አንቀጽ 44 ዜጎች ጽዱና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው በሚል በተቀመጠው መሰረት ከተሞችን ጽዱና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚደረገው እንቅስቃሴ ለልማትና ለሕብረተሰቡ ዕድገት ጠቃሚ ነው። በመሆኑም በአንድ ቦታ የተከናወኑ መልካም ስራዎችን በተሞክሮነት ቀምሮ ሌሎች እንዲማሩበትና እንዲጠቀሙበት ማድረግ ተገቢ ስለሆነ ይህን የመልካም ተሞክሮ ሰነድ ቀምሮ ለሌሎች እንዲስፋፋ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

1.3. ወሰን

የተሞክሮ ቅመራው የተከናወነው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የተከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የኮሪደር ልማት ስራ ተግባራት በአሰራር ውጤታማና ማሳያ(ሞዴል) ሆነው በተገኙ ስራዎች ላይ ያተኮረ ነው።


1.4. የመረጃ አሰባሰብ ስልት

በመጀመሪያ ተሞክሮን ለማሰባሰብ የሚረዳ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት አስቀድሞ ለክልልና ለከተማ አስተዳደሩ በኢሜል በመላክ ይዘቱን ቀድመው እንዲያውቁት ተደርጓል። በመቀጠልም የባለሙያዎች ቡድን በሥራው ላይ እንደተሠማራ በቅድሚያ ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና ከከተማ አስተዳደሩ አካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ማዘጋጃ ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ስለ ተልዕኮው ዝርዝር ሁኔታ በመወያየት የተሻለ ተሞክሮ የሚገኝበት ተብሎ በተመረጠው ቢሾፍቱ ከተማ ውስጥ በመንቀሳቀስ መረጃ ተሰባስቧል።

መረጃ አሰባሰቡም የተዘጋጀውን ቼክ ሊስት በመጠቀም ሲሆን ለዚሁ ተግባር የሚጠቅሙ ሰነዶችን በማገላበጥ፣የማህበር አባላትን፣ሌሎች ተጠቃሚዎችንና ባለሙያዎችን በማነጋገር እና ሥራው በሚከናወንበት ቦታ ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል።

በማጠቃለያውም ከቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃና አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመስክ ምልከታው በታዩና በተነሱ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት ተደርጎ ተጨማሪ መረጃ ተወስዷል።








ፎቶ ፡- በተለያየ ስልት መረጃ ሲሰበሰብ

2. ክፍል ሁለት

2.1. ቢሾፍቱ ከተማ

የቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሲሆን ከተማው የተመሠረተው በ1917 ዓ.ም.የኢትዮ-ጂቡቲ ባቡር መሥመር መስፋፋትን ተከትሎ ነበር። ከተማው ከአዲስ አበባ በ47 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በሰሜን ሸገር (ገላን ክ/ከተማ)፣ በደቡብ ሉሜ ወረዳ፣ በምስራቅ አደአ ወረዳ እና በምዕራብ ሊበን ወረዳ ያዋስኑታል። የከተማው አየር ፀባይ ወይነደጋ ሲሆን አማካይ ከፍታ ከባህር ወለል በላይ 1,858 ሜትር ሆኖ አማካይ ወርሐዊ የሙቀት መጠንም ከ22.1 እስከ 30.2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ነው። የቢሾፍቱ ከተማ ከ1983 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ የአደአ ወረዳ ዋና ከተማ ሆኖ አገልግሏል። በመቀጠልም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የመጀመሪያ ደረጃ ከተማ አስተዳደር ሆኖ በከንቲባ መመራት ችሏል። ከዚያም ከተማው እያደገ በመሄድ ሰፋፊ አገልግሎቶችን መስጠት ቀጥሎ የከተማ መዋቅሩ እየተስፋፋ መሄድ ችሏል። በከተማው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርም እየጨመረ መቷል።

የዚህም ዋንኛ ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ እና ከሌላ ከተማ በፍልሰት የሚመጡ ሰዎች በመኖራቸው ነው። አሁን ከከተማ አስተዳደሩ በተገኘ መረጃ መሰረት የቢሾፍቱ ሕዝብ ብዛት ወ 272565 ሴ 250304 ድ 522869 ሲሆኑ በመንግስት ሰራተኝነት ፣በንግድ እና በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ናቸው። ቢሾፍቱ ከተማ የኢንዱስትሪ እና የቱሪስት ማዕከል ከሆኑት ከተሞች ውስጥ አንዱ ሲሆን ታዋቂ የሆኑ የ7 ሀይቆች ማለትም የሆራ አርሰዲ፣ የባቦጋያ፣የቢሾፍቱ፣ የጨለለቃ፣ የኪሎሌ፣ የኩሪፍቱ እና የመገርሳ ሀይቆች መገኛ ነው። የዕጽዋት ሽፋኑን ስንመለከት ባሁኑ ጊዜ በከተማው መንገዶች ዳር የተለያዩ ዝርያ ያላቸው ችግኞችን የመትከል እንቅስቃሴም ተጠናክሮ እየቀጠለ ነው።ይህ ከተማ በተለይ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የኮሪደር ልማት ስራ እየተፋጠነ ስለሆነ የከተማው እድገት እና ውበት እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል።




ፎቶ 2፡- የቢሾፍቱ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ የሚገኝበት ህንጻ

2.2. በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ከመጀመሩ በፊት አካባቢው የነበረበት ሁኔታ

በፊት የቢሾፍቱ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ችግር ያለበት ሆኖ ይገኝ ነበር። ለዚህም መነሻ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ከፍተኛ መሆን፣ የከተማን አኗኗር በአግባቡ ያለመለማመድ፣ የአመራር ትኩረት ማነስ፣ ከተሞቻችንን የሚመጥን እድገትን መሰረት ያደረገ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ያለመዘርጋት የመሳሰሉ ናቸው።

በቢሾፍቱ ከተማ ቀደም ሲል የነበረው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ያለጥንቃቄ በዘፈቀደ የሚደረግ ነበር። ከቤት ለቤት እንዲሁም ከተለያዩ ሆቴሎችና ሌሎች ንግድና ማምረቻ ተቋማት ይወጣ የነበረው ደረቅ ቆሻሻ የከተማውን ገጽታ ከማበላሸቱም በላይ የአየር ብክለት በመፍጠር ከፍተኛ የጤና ጠንቅ ሆኖ ነዋሪዎችን በእጅጉ ይጎዳ እንደነበር እንዲሁም እንስሳቶች የወዳደቁ ፌስታሎችን እየበሉ ለሞት እየተጋለጡ ነበር። በዚያን ወቅት የነበረ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ጥርቅም የወባ ትንኝ እንዲራቡ ምክንያት ሆኖ ነዋሪዎች ለወባ በሽታ የተጋለጡበት ወቅትም ነበር።

በተጨማሪም ቆሻሻ ማስወገጃና ማጠራቀሚያ ቦታዎች በበቂ ሁኔታና በጥንቃቄ ያልተደራጁ በመሆኑ የሚመነጩ ቆሻሻዎች በየመንገዱና በመኖሪያ መንደሮች ሥርዓት በሌለው ሁኔታ በየቦታው በባቡር ሀዲድ ላይ ጨምሮ ይጣል ነበር።ይህም ከፍተኛ የህዝብ ቅሬታ ሲፈጥር ቆይቷል። በተጨማሪም በየመንገዱ የሚገኙ ቦዮች በየጊዜው ስለሚደፈኑ በዝናብ ወቅት መንገዶች በጎርፍ እየተጥለቀለቁ ለመተላለፍ ያስቸግሩ ነበር። ሕብረተሰቡ ቆሻሻን ለማጽዳት ኃላፊነቱን የሚወስደው አንድ ድርጅት ብቻ(ማዘጋጃ ቤት) ነው ብለው ያምኑ ስለነበር አካባቢን በማጽዳት አይመለከተኝም የሚል እሳቤ ነበራቸው። ከግንዛቤ እጥረት የተነሳም ቆሻሻ ጉዳት ብቻ እንጂ ምንም ጥቅም እንደሌለው አድርገው ያስቡ ነበር።

በመሆኑም ይህንን ችግር ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል።በየቦታው ገንዳዎች በማስቀመጥ ነዋሪዎች እንዲጠቀሙ ተደርጎ ነበር። ይሁን እንጂ ሁኔታው ሊሻሻል አልቻለም ነበር።ይህንንና መሰል የቆሻሻ አያያዝ ሥርዓትን ለማሻሻልና ፈር ለማስያዝ የከተማ አስተዳደሩ የተሻለ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት ሲያደርግ በመቆየቱ ከጊዜ ጊዜ ተጨባጭ ለውጥ መታየት ጀምረዋል።

2.3. የቆሻሻ አያያዝና አወጋድ ችግሮችን ለመፍታት የተከናወኑ የግንዛቤ ሥራዎች

በፊት ከተለመደው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ተላቆ ትክክለኛ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ለመፍጠር በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ አካላት የግንዛቤ መፍጠር ስራ ተሰርቷል።ግንዛቤው የተፈጠረው ለከተማ አመራሮች፣ለቀበሌ አመራሮች፣ለጎጥ አመራሮች ፣ለጥቃቅንና አነስተኛ/ማህበራት፣ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች ሲሆን በአጠቃላይ ከ2011-2012 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ወ 752 ሴ 246 ድ 998 ሰዎች ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ሲሆን ይህ ግንዛቤ የተፈጠረው የናማ ፕሮጀክትን በመጠቀም ነው። እንዲሁም በዚሁ ፕሮጀክት ድጋፍ አማካይነት ለ40 ሰዎች ስልጠና ተሰጥቶ ደረጃ /Level/2 በመመረቅ ሰርተፊኬት ተሰጥቷቸው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል።

በ2016 ዓ.ም በተለያዩ ርዕሶችና ደረጃዎች ግንዛቤ የተፈጠረ ሲሆን በግንዛቤው ወ 118775 ሴ 127305 ድ 246080 ሰዎች ተሳትፈውበታል። በሌላ በኩል መጽሔት፣ብሮሸርና በራሪ ወረቀት በማዘጋጀት ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።ሚዲያ አጠቃቀምን በተመለከተ ቴሌቪዥን፣ሬዲዮ ፋናን እና ኦቢኤን ሬዲዮ በመጠቀም ለህብረተሰቡ ግንዛቤን ማድረስ ተችሏል።

2.3.1. በግንዛቤ የተገኘ ለውጥ

የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ስርአት ለማስያዝ የግንዛቤ መፍጠር ስራዎችን አከናውኖ በሕብረተሰቡ አስተሳሰብ ላይ የተሻለ ለውጥ አምጥቷል።ህብረተሰቡ በፊት ከነበረው አስተሳሰብ ተላቅቆ ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ተገንዝቧል።ቆሻሻ ከአካባቢው እንዲነሳለት የሚጠይቅ ማህበረሰብ ተፈጥሯል።ሌሎች ቆሻሻ ያለአግባብ ሲጥሉ ሲያይ ጥቆማ መስጠትም ጀምሯል።ማንኛውም ሰው ላመነጨው ቆሻሻ መክፈል እንዳለበት አምኖበታል።ደረቅ ቆሻሻ ሀብት መሆኑን በመረዳትም የተገኘውን ግንዛቤ ወደ ተግባር በመቀየር የመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ችሏል።በተለይ በሞዴል መንደር ያሉ ነዋሪዎች ያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ በየአይነቱ በመለየት መልሶ መጠቀም እና ለሚሰበስቡ ማህበራት በአግባቡ ማስረከብ ችለዋል።በአጠቃላይ የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ አያያዙና አወጋገዱ ስርአት ስለያዘ የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ባለመያዝ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ቀንሰዋል።

2.4. የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

በ2000 ዓ.ም ከተማው በተወሰነ መልኩ ጥቃቅንና አነስተኛን በማደራጀትና በማስተባበር ደረቅ ቆሻሻ ከየቦታው በእጅ በሚገፋ ጋሪ እየተሰበሰበ ቁጥጥር በሌለበት ማስወገጃ ቦታ (open area) በሆነው ጎልባ በሚባል ቦታ መጣል ተጀመረ።

ከጊዜ ጊዜ ሕብረተሰቡ እየበዛ፣ የሚፈጠር ቆሻሻም እየጨመረ ሲመጣ እና በቆሻሻው ምክንያት እየተፈጠረ ያለው የጤና ችግር ከፍተኛ እየሆነ ሲመጣ መፍትሔ መፈለግ ግድ ሆነ::በመሆኑም በ2001 ዓ.ም የከተማ አስተዳደሩ በCRGE በጀት በተዘጋጀ ገንዳ የመጠቀም ስርዓት ፈጥሮ ገንዳው ከመኖሪያ ቤት 200ሜ እና ከመንገድ 4ሜ ርቀት እንዲቀመጥ ተደርጎ በየቦታው መንጭቶ የሚሰበሰብ ደረቅ ቆሻሻ በገንዳ ውስጥ እንዲሰበሰብ ተደረገ:: ገንዳውም በስኪፕ ሎደር እየተነሳ ቁጥጥር በሌለበት ማስወገጃ ቦታ(open area) በሆነው ጎልባ በሚባል ቦታ መጣል ተጀመረ::ይህ ቢደረግም ከሕብረተሰቡ ግንዛቤ ማነስ የተነሳ ውስጥ ሳይገባ በገንዳው ዙሪያ ቆሻሻው ተጥሎ አካባቢውን መበከል ቀጠለ:: ለዚህም መፍትሔ ያሸዋል በሚል ገንዳው ከመነሳቱ በፊት የተዝረከረከውን የሚሰበስቡ የቀን ሰራተኞች በመጠቀም የከተማው ማዘጋጃ ቤት ማሰራት ጀመረ::አሁንም የቆሻሻው መጠን እየጨመረ በመሄዱ ያለው ማጓጓዣ በቂ አልነበረም::ይህንን በማየት የከተማው ማዘጋጃ መፍትሔ የማፈላለግ ጥረቱን ቀጠለ::በ2006 ዓ.ም በተሻለ ሁኔታ ጥቃቅንና አነስተኛን በማደራጀት በCRGE በጀት የተገዙ 4 የደረቅ ቆሻሻ ማመላለሻ ባጃጅ በስጦታ እና ማዘጋጃ ዋስትና ወስዶ ከአዳማ ትራክተር ፋብሪካ በ5 ዓመት ክፍያ ለመጨረስ በዱቤ 2 ትራክተር ተዘጋጅቶ ስራው ተጠናክሮ እንዲሰራ ተደረገ::ይህም የተደረገው የከተማው አስተዳደር ከችግሩ ለመላቀቅ ያለው ጥረት ታይቶ ነው::

ይህንኑ የከተማው አስተዳደር እንቅስቃሴ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለውን ለውጥ በማየት NAMA ከሚባል ፕሮጀክት ተጨማሪ ትራክተሮች እና ስኪፕሎደር በስጦታ ተገኘ:: በፊት በዱቤ የተገዛው ትራክተር እዳ ሲጠናቀቅ በ2013 ዓ.ም ተጨማሪ ሌሎች ትራክተሮች አሁንም በማዘጋጃ ዋስትና እንዲመጣ ተደረገ::

ቁጥጥር የሌለበት ማስወገጃ በሆነው ጎልባ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታ ላይ ከሕብረተሰቡ የተለያየ ቅሬታ ስለቀረበ እና የከተማው ማዘጋጃም ችግሩን ገምግሞ ቦታው መቀየር እንዳለበት ስላመነ ውሳኔ ላይ ተደረሰ:: ከውሳኔው በመነሳት ጥናት ተጠንቶ ጋራ በሩ በሚባል ቦታ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ደረጃን በጠበቀ መልኩ እንዲሰራ ተወስኖ ስራው ተጀመረ::

2.5. የተሟሉ ግብዓቶችና የቴክኖሎጂ ውጤቶች

በከተማው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን ለመተግበር የሚያገለግሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ፣ትራክተር፣ግሬደር፣ስኪፕ ሎደር፣ስካባተር፣ዶዘር፣ሮሎ እና ቀልዝ መገልበጫ ማሽን የመሳሰሉ ሲሆን ባለቤትነቱም የከተማው ማዘጋጃ ነው::እነዚህ ግብዓቶች ለመሰረተ ልማት ማከናወኛ እና ለዚሁ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት መተግበሪያ በማገልገል ላይ ይገኛሉ::





ፎቶ 3፡- ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ማከናወኛ የሚያገለግሉ ማሽነሪዎች

2.6. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ ማሕበራት

በቢሾፍቱ ከተማ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ 67 ማህበራት ያሉ ሲሆን ቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብ፣ደረቅ ቆሻሻ የመለየት፣የኮምፖስት ዝግጅት እና የመንገድ ላይ ጽዳት የሚሰሩ ማህበራት ናቸው:: እነዚህ ማህበራት ሁሉም የየራሳቸው አባላት አሏቸው::

ቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የሚያሰባስቡ ማህበራት ብዛት 25 ሲሆኑ ወ 145 ሴ 105 ድ 250 አባላት አሏቸው::ደረቅ ቆሻሻ የመለየት ስራ የሚሰሩ ማህበራት ብዛት 14 ሲሆኑ የአባላት ብዛት ወ 28 ሴ 112 ድ 140 ናቸው::የኮምፖስት ዝግጅት ማህበራት ብዛት 3 ሲሆኑ ወ 24

ሴ 6 ድ 30 አባላት አሏቸው።የመንገድ ላይ ጽዳት ማህበራት ብዛት 25 ሲሆኑ የአባላት ብዛት ወ 20 ሴ 238 ድ 258 ናቸው።በአጠቃላይ 67 ማህበራት ያሉ ሲሆን ወ 217 ሴ 461 ድ 678 አባላት በዚህ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ተግባር ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ከነዚህ አባላት በተጨማሪ መንግስት በኮንትራት የቀጠራቸው 78 ሰራተኞች ስላሉ እነዚህን በመጠቀም በመንግስት ተቋማት እና በመንገድ ላይ የተሰበሰበ ደረቅ ቆሻሻን የማስነሳት ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

2.7. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ

በየግለሰቡ ቤት የሚገኘው ደረቅ ቆሻሻ መጀመሪያ ሁሉም ነዋሪ በየቤቱ ደረቅ ቆሻሻውን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢት(በማዳበሪያ) በግቢያቸው እንዲያጠራቅሙ ይደረጋል።በመቀጠል ቤት ለቤት በሚሰበስቡ ማህበራት በሳምንት አንድ ጊዜ በተመደቡበት ሳይት/ ቦታ በየቤቱ በመንቀሳቀስ የተጠራቀመውን ደረቅ ቆሻሻ በማንሳት ወደ ጊዜያዊ ደረቅ ቆሻሻ መቀባበይ ቦታ ያደርሳሉ።የተሰባሰበው ቆሻሻ መነሳት ያለበት በሳምንት ሁለት ጊዜ በሚል ውል የተዋዋሉ ቢሆንም በየግለሰቦቹ ቤት የሚጠራቀመው ቆሻሻ በጣም አነስተኛ ስለሆነ በሳምንት አንድ ጊዜ በሚል ስምምነት ላይ ተደርሶ ወደ ተግባር ተገብቷል።በግል ተቋማት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻም የሚነሳው በነዚሁ ማህበራት አማካይነት ነው።የማንሻ ጊዜውም እንደ ሁኔታው ሲሆን የሆቴሎች በየቀኑ ይነሳል።በመንገድ ላይ የሚያጸዱ ማህበራት ደረቅ ቆሻሻውን ከሰበሰቡ በኋላ በየቦታው የተሰበሰበው ደረቅ ቆሻሻ በዚያኑ እለት የኮንትራት ሰራተኞችን በመጠቀም በማዘጋጀ ይነሳና ወደ ጊዜያዊ ደረቅ ቆሻሻ መቀባበያ ቦታ እንዲደርስ ይደረጋል። በተጨማሪም በመንግስት ተቋማት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ የሚነሳው በማዘጋጀ ቤት አማካይነት ሆኖ የማንሻ ጊዜው እንደ ቆሻሻው ብዛት ሁኔታ ታይቶ ነው።

2.7.1. የክፍያ ሁኔታ

ይህ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ሲጀመር ማዘጋጀ ከማህበራት ጋር ውል ተዋውሎ ሲሆን ሕብረተሰቡም ድርሻው ምን እንደሆነ እና ይህንኑ መወጣት እንዳለበት ግንዛቤ ተፈጥሮለት ነው።በመሆኑም ሁሉም ማሕበራት እንደየ ስራ ድርሻቸው ግዴታቸውን ሲወጡ የህብረተሰቡ እና የተቋማት ግዴታ ከሆነው ውስጥ አንዱ ደግሞ ወርሀዊ ክፍያ ነው።በዚህ መሰረት አንድ አባወራ በወር 70 ብር፣ሆቴሎች ከ2000-3000 ብር፣ ትናንሽ ቁርስ ቤቶች/ተቋማት ከ200-300 ብር በወር ይከፍላሉ።ከመንገድ ላይ እና ከመንግስት ድርጅት ቆሻሻ የሚነሳው በማዘጋጀ ስለሆነ ክፍያ የለውም።በተለያዩ ፕሮግራሞች ምክንያት የተለየ ቆሻሻ ከመነጨ ደግሞ በስምምነት በልዩ ክፍያ ይነሳል።

2.7.2. ደረቅ ቆሻሻን በየአይነቱ የመለየት ስራ

የደረቅ ቆሻሻ የመለየት ስራው የሚከናወነው በሞዴል መንደር በየቤቱ ነው።ከሌሎች መንደር እና ከተቋማት የመነጨ ደረቅ ቆሻሻ በጊዜያዊ መቀባበያ ቦታ የመለየት ስራ ይሰራና ተፈላጊ የሆነው ወደሚፈለገው ቦታ ይላካል።የማይፈለገው ደግሞ ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዲላክ ይደረጋል።





ፎቶ 4፡- ደረቅ ቆሻሻ የመለየት ስራ ሲከናወን

2.7.3. የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ መቀባበያ ቦታዎች

በቢሾፍቱ ከተማ 3 የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ መቀባባያ ቦታዎች አሉ::እነሱም

1. ቢፍቱ ወረዳ
2. ደከ ቦራ ወረዳ
3. ሆራ ወረዳ ናቸው

እነዚህ የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ መቀባበያ ቦታዎች የሚመጣውን ደረቅ ቆሻሻ የመረከብና የመለየት ስራ በመስራት ወደሚፈለገው እና ወደ ማስወገጃው ቦታ ያስተላልፋሉ::ተመልሰው ለሌላ አገልግሎቶች የማይውሉ የግንባታ ፍርስራሾች የደረቅ ቆሻሻ ጊዜያዊ መቀባበያ ቦታ ሳይደርሱ በቀጥታ ወደ ማስወገጃ ቦታ ተወስደው ይጣላሉ::







ፎቶ 5፡-ጊዜአዊ መቀባበያ ቦታ

2.8. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill)

በቢሾፍቱ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ (sanitary land fill) ይገኛል:: ማስወገጃ ቦታው የሚገኘውም ከሕብረተሰቡ መኖሪያ 5 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ሲሆን ‘‘ጋራ በሩ’’ በሚባል ቦታ ላይ ነው:: ይህ ቦታ ክልል ስፋቱ 11 ሄክታር ነው::

ቀደም ሲል ቁጥጥር የሌለበት ማስወገጃ ቦታ (open dump area) በሆነው ጎልባ በሚባል ቦታ ደረቅ ቆሻሻው ሲጣል የነበረው እስከ ጥቅምት/2011 ዓ.ም ነበር::ከሕዳር/2011 ዓ.ም ጀምሮ ግን የጋራ በሩ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) አገልግሎት መስጠት ጀመረ::ይህ ቦታ ተመርጦና ተሰርቶ ስራ እንዲጀምር የተደረገው በጥናት ስለሆነ አሁን ባለበት ሁኔታ የቀረበበት ቅሬታ የለም::አገልግሎት አሰጣጡም እስከ 20 ዓመታት ተብሎ ስለታሰበ በዚሁ መሠረት አገልግሎት እንዲሰጥ የከተማው መዘጋጃ ተገቢውን

ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ይገኛል። በዚህ ቦታ የተለያየ የስራ ድርሻ ያላቸው የሰው ኃይል አሉ።እነሱም በጥበቃ፣በአስተባባሪነት እና በመረጃ መያዝ ስራ ላይ የተሰማሩ ሲሆን ወ 4 ሴ 3 ድ 7 በቦታው ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ናቸው።ይህ ቦታ በመንግስት ባለቤትነት የሚተዳደር ነው።በቦታው ላይ በፊት የነበሩ የተፈጥሮ ዛፎች እንከብካቤ እየተደረገላቸው ሲሆን በተጨማሪም የአየር ብክለትን ሊቀንሱ የሚችሉ ዕጽዋት ተተክለዋል።





ፎቶ 6፡- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ግቢ

ካሉት 3 የደረቅ ቆሻሻ መቀባበያ ቦታዎች ውስጥ አንዱ በሆራ ወረዳ የሚገኘው በዚህ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) ክልል ውስጥ ሲሆን 400 ካ.ሜ ስፋት ይዞ ተግባሩን እዚሁ በቅርበት እያከናወነ ይገኛል።በትራክተር ተጭኖ የሚመጣው ደረቅ ቆሻሻ ስንት ሜትር ኩብ እና ኪሎግራም እንደሆነ መጠኑን የመመዝገብ ስራ በቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) ግቢ ውስጥ ይሰራል።የስራ ክንውኑም በየወሩ ለሚመለከተው ሪፖርት ይደረጋል።

የቀልዝ(ኮምፖስት) ማዘጋጀት ማህበራትም የሚገኙት በዚሁ ክልል ውስጥ ነው።እነዚህ ማህበራት በተዘጋጀላቸው ሼድ ውስጥ ሆነው ተግባራቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ።






ፎቶ 7፡-ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ

2.9. ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

በቢሾፍቱ ከተማ የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን ለመጠቀም ሲባል ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ተችሏል፡፡ይህ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ስርዓትም ቆሻሻው በአግባቡ እንዲወገድ እና ጥቅም መስጠት የሚችል አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡እንዲሁም ቆሻሻ በአግባቡ ከተያዘና ከተጠቀሙበት ሀብት እንደሆነ በተግባር እንዲታይ ረድቷል፡፡

በቢሾፍቱ ከተማ ማዘጋጃ አስተባባሪነት ማህበራትን በማቋቋም ወደ ስራ የማስገባት ስራ ተሰርቷል፡፡ከ2012-2013 ዓ.ም ቀለሙ ቀይ፣ቢጫ፣አረንጓዴ የሆኑ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢት(ማዳበሪያ) እና ባልዲ የከተማው ማዘጋጃ ገዝቶ ለሞዴል መንደሮች ቤት ለቤት በማከፋፈል እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ(ኮምፖስት) በማዘጋጀት ለተጠቃሚ ማስረከብ ተችሏል፡፡ከናማ(NAMA) ፕሮጀክት የተገኘ ኮምፖስት የሚገለብጥ ማሽን በመጠቀም በአካፋ ይገለበጥ የነበረን ኮምፖስት በማሽኑ በመገልበጥ ስራውን ፈጣንና ቀልጣፋ ማድረግ ተችሏል፡፡ፕላስቲክን መልሶ/አሻሽሎ መጠቀም እንደሚቻል በማወቅ እንዲሁም ከሞራ ሳሙና እንደሚሰራ፣ ከአጥንት የዶሮ መኖ እንደሚሰራ፣ ከቀንድ ጌጣጌጥ፣ማንኪያ እና ዋነንጫ እንደሚሰራ በማወቅ ከሌሎች ቆሻሻዎች ውስጥ ለብቻ በመለየት ለተረካቢዎች እያስረከቡ ይገኛሉ፡፡

2.10. የሥራ ዕድል ፈጠራ

በተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስራ ላይ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ወጣቶችና ሴቶች ናቸው፡፡ በዚህም ወ 221 ሴ 515 ድ 736 ወጣቶች በስራው በመሳተፍ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በአረንጓዴ ቦታዎቾች ልማት፣ የመሳሰሉት ስራዎች የከተማው ማዘጋጃ ለሴቶች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

2.11. ቅንጅታዊ ስራ

የከተማው ማዘጋጃ እና አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ዕቅዳቸውን በጋራ በማቀድ ስራውን በጋራ እየሰሩ ክትትልና ቁጥጥር እያደረጉ የስራውን ቀጣይነት እያጠናከሩ ይገኛሉ፡፡

2.12. በተከናወኑ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ እንዲሁም በውበትና መናፈሻ ስራ ውስጥ በመልካም ተሞክሮነት የሚወሰዱ

2.12.1. ሞዴል መንደር

በቢሾፍቱ ከተማ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንዲሁም አካባቢያቸውን በጽዳት በመያዝና በማልማት እንቅስቃሴአቸው ታይቶ 16 ሞዴል መንደሮች ተመርጠዋል፡፡በእነዚህ ሞዴል መንደሮች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ራሳቸውን በማደራጀት ወደ ልማት በመሰማራት፣አካባቢያቸውን በጋራ በፕሮግራም በየሳምንቱ በማፅዳት፣የሚነገራቸውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተቀብለው በመጠቀም፣በግል

ግቢያቸው ውስጥ የአረንጓዴ ልማት በማልማት እና ለሌሎች መንደሮች አርአያ ሆነው ስለተገኙ ሞዴል መንደር ተብለው ሊመረጡ ችለዋል።ከተመረጡት ሞዴል መንደሮችም ውስጥ ሦስቱ የሚከተሉት ናቸው።

2.12.1.1. ዝቋላ መንደር

በዚህ መንደር ‘‘ለመንደሬ ጽዳት ሀላፊነት አለብኝ’’ የሚል መሪ ቃል ተዘጋጅቶ እና ተፅፎ በመንደሩ በተቀመጠው ታፔላ ላይ ይታያል።በአካባቢው ያሉ መንገዶች ጽዳታቸው የተጠበቀ ነው።በየአጥሮቹ ዳርቻ የተለያዩ አረንጓዴ ተክሎች ተተክለው ለመንደሩ ውበት ሆነዋል።የግለሰቦቹ ግቢ ጽዳቱ የተጠበቀ ነው።የመነጨ ደረቅ ቆሻሻ እስኪነሳ ድረስ በደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢት(በማዳበሪያ) የሚበሰብስ እና የማይበሰብስ በሚል በየአይነቱ ተለይቶ ይቀመጣል።ከሚበሰብሱ ቆሻሻዎች ቀልዝ(ኮምፖስት) በማዘጋጀት ለግቢያቸው ችግኝ የሚጠቀሙም አሉ።በግቢያቸው ውስጥ የተለያዩ ተክሎች አልምተዋል።ለምሳሌ በአቶ ሸገና ደምሴ ግቢ ውስጥ ቡና፣ሎሚ፣ዘይቱና፣ኮባ፣እንጆሪ፣ሰላጣ፣አባጮማ፣ንመን፣ጌሾ፣የሾርባ ቅጠል እና ሌሎችም በርካታ የእፅዋት ዝርያዎች በግቢው ውስጥ ይገኛሉ። አቶ ሸገና ደምሴ ከባለቤታቸው ወ/ሮ ሸዋለም ነጋሽ ጋር በመሆን ‘‘ቆሻሻን ወደ ሀብት’’ በማለት ዩቲዩብ(you tube) ከፍተዋል።በዚህ አባወራ ግቢ የሚበሰብስ ቆሻሻ በዚያው ግቢ ውስጥ ቀልዝ(ኮምፖስት) ስለሚሰራ ለማህበራት የሚያስረክቡት የማይበሰብስ ቆሻሻ ብቻ ነው።ወ/ሮ ሸዋለም ነጋሽ የቤት እመቤት ሲሆኑ በግቢያቸው ልማቱን ከጀመሩ 3 ዓመት እንደሆናቸው እና ትምህርቱን ያገኙት ከማዘጋጃ እና ከአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች ነው።












ፎቶ 8፡- በአቶ ሽገና ደምሴ እና በወ/ሮ ሸዋለም ነጋሽ ግቢ ያለ ልማት

2.12.1.2. አዳ መንደር

የአዳ መንደር ነዋሪዎች አካባቢያቸው ጽዱ ከመሆኑ ተጨማሪ የጋራ የሆነ የተከለለ የአረንጓዴ ልማት ቦታ (ግሪን ኤሪያ) አላቸው።ይህ ቦታ በፊት ማንም ያለአግባብ ቆሻሻ ይጣልበት ነበር።በመሆኑም አካባቢው ከመበከሉ የተነሳ ለነዋሪዎቹ ብቻም ሳይሆን በአካባቢው ለሚተላለፉም ሰዎች ከፍተኛ የጤና ጠንቅ ሆኖ ነበር።የመንደሩ ነዋሪዎች በጋራ በማጽዳት እና የተለያዩ ችግኝ በመትከል አልምተው በአጥር በመከለል አስከብረውታል።በልማቱ ስራም የጎጥ ኃላፊ እያስተባበረ ከወረዳም ክትትልና ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።








ፎቶ 9፡- የአዳ መንደር

2.12.1.3. ሰላም መንደር

በዚህ መንደር ‘‘ሀገሩን የሚወድ አካባቢውን ይጠብቃል’’ የሚል መሪ ቃል ተዘጋጅቶ እና ተፅፎ በመንደሩ በተቀመጠው ታፔላ ላይ ይታያል፡፡መንገደኛ በአካባቢው ሲያልፍም መጠቀም እንዲችል በማለት የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት(ባስኬት) በመስመር ላይ ተቀምጧል፡፡በመንደሩ ከሚኖሩ ነዋሪዎች ውስጥም የጽዳት ውበት አምባሳደሮች በሚል 16 ሰዎች ተመርጠዋል፡፡አካባቢያቸው ጽዱ ከመሆኑ ተጨማሪ የጋራ የሆነ የተከለለ የአረንጓዴ ልማት ቦታ (ግሪን ኤሪያ) አላቸው፡፡የዚህ አረንጓዴ ልማት ቦታ (ግሪን ኤሪያ) ባለቤት 97 አባወራዎች ናቸው፡፡ በዚህ ውስጥ 9 የልማት ቡድኖች አሉ፡፡ እነዚህ ነዋሪዎች ቦታው እንዲሰጣቸው መንግስትን በመጠየቅ የተሰጣቸው ሲሆን ቦታው ተከልሎ መልማት የጀመረው በ1997 ዓ.ም ነው፡፡

ይህ ቦታ በፊት ያለአግባብ ቆሻሻ ይጣልበት ነበር፡፡አሁን ግን የመንደሩ ነዋሪዎች በጋራ በማጽዳት አልምተው በአጥር በመከለል አስከብረውታል፡፡በልማቱ ስራም የቡድን መሪዎች እያስተባበሩ ከወረዳም ክትትልና ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ይህ ቦታ የመስቀል በአል ማክበሪያ፣የልጆች ምርቃት ማከናወኛ፣የሰርግ ፕሮግራም ማከናወኛ፣አንዳንድ የሽልማት ፕሮግራም ማከናወኛ እና የተለያዩ ፕሮግራሞች መወያያ በመሆን የአረንጓዴ ልማት (ግሪን ኤሪያ) ቦታ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡የጽዳት ፕሮግራም በየሳምንቱ ቅዳሜ ሲሆን ከጽዳት ስራ የቀረ 1500 ብር ይቀጣል፡፡ በአካባቢው ቆሻሻ ሲጥል የታየ እስከመታሰር በሚል በመስማማት ወስኗል፡፡ ቅዳሜ የጽዳት ቀን ስለሆነ ጠዋት ከ12፡00 እስከ 1፡30 በአካባቢው ሱቅ እንዳይከፈት ወስኗል፡፡









ፎቶ 10፡- የሰላም መንደር

2.13. ቀልዝ (ኮምፖስት) የሚያዘጋጁ ማህበራትና ዝግጅት

የቢሾፊቱ ከተማ ቀልዝ(ኮምፖስት) የሚዘጋጀው በቆሻሻ ማስወገጃ /Sanitary Land Fill/ ግቢ ውስጥ ነው። የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በቢሾፍቱ ከተማ ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳሉ ተብለው ከተቋቋሙ ማህበራት ውስጥ ሦስቱ ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ(ኮምፖስት) የሚያዘጋጁ ማህበራት ናቸው።እነሱም ሀዊ ቦሩ ማህበር፣ነጌኛ ማህበር እና ሆራ ማህበር ናቸው።እነዚህ ሦስቱም ማህበራት እየሰሩ ያሉት ጎን ለጎን በአንድ ሼድ ውስጥ ሲሆን የሦስቱም የአሰራር ስርአታቸው ተመሳሳይ ነው።ማህበራቱ ከተቋቋመ 5 ዓመት ሆኗቸዋል።የቀልዝ(የኮምፖስት) የመገልበጥ ስራው የሚከናወነው እንደበፊቱ በአካፋ ሳይሆን አሁን በዘመናዊነት የሚገለብጥ በማሽን በመጠቀም ነው።የቀልዝ(የኮምፖስት) ስራው ተጀምሮ ለተፈለገው ጥቅም እስኪውል ድረስ 3 ወራት ይፈጃል።

የቀልዙ (የኮምፖስቱ) የመገልበጫ ወቅት የሚወሰነው በሙቀቱ መጠን ነው።የሙቀት መለኪያ መሳሪያ ስላላቸው ሙቀቱ ተለክቶ 50 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲደርስ ይገለበጣል።ለአገልግሎት የደረሰውን ቀልዝ (ኮምፖስት) የሚያስረክቡት ለማዘጋጃ እና ለአረንጓዴ ልማት ቦታ ማህበር ሲሆን 1 ኪ.ግ በ3.50 ብር ያስረክባሉ።









ፎቶ 11፡- ቀልዝ (ኮምፖስት) በሼድ ውስጥ ሲዘጋጅ

2.14. የኮሪደር ልማት ስራ

የኮሪደር ልማት የመንገድ መሠረተ ልማትን በማሻሻል ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶችን በግራና በቀኝ ደረጃውን የጠበቀ ማድረግ፣የብስክሌት ማሽከርከሪያ መንገድ መፍጠር፣በርካታ መኪናዎችን ማስተናገድ የሚችሉ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያዎችን (ፓርኮችን) መገንባት፣የአውቶቡስና የታክሲ ማቆሚያ ተርሚናሎችን ማመቻቸት የመሳሰሉ ተግባራትን ያቀፉ ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው።

በሌላ በኩልም የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ሥራዎች ማዘመን ሲሆን ስክሪንና የደህንነት ካሜራ ያላቸው ስማርት ፖሎች፣መደበኛ የመንገድ መብራቶችና ነባር የኤሌክትሪክ መሥመር ፖሎችን አንስቶ ምድር ውስጥ የመቅበር ሥራ የመሳሰሉትን የማፋጠን ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተጨማሪም የህዝብ መዝናኛዎችንና ማረፊያዎችን፣የውሃ ፏፏቴዎችን፣ዘመናዊ የመንገድ ዳር መፀዳጃ ቤቶችን በጥናት የመገንባት ሥራንም የሚያጠቃልል ነው።እንዲሁም

የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችም በስፋትና በትኩረት የሚፈፀሙ ሲሆን የውሃ ፍሳሽ ማስወገጃዎችና የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት ሥራዎችም በፕሮጀክት ሥራው ሰፊ ግምት ያገኙ ናቸው።

በዚሁ መሠረተ በቢሾፍቱ ከተማ ሰፊ የኮሪደር ልማት ስራዎች ተጀምረው እየተሰሩ ይገኛሉ።በመሆኑም 13 ሳይቶች/ቦታዎች ተመርጠው በሁለት ዙር ለማልማት ታቅዶ በ1ኛ ዙር 7 ሳይቶች ላይ ስራው ተጀምሮ ልማቱ እየተከናወነ ይገኛል።በ2ኛው ዙር 6 ሳይቶች ለማልማት የታቀደ ሲሆን ልማቱ የሚቀጥል ይሆናል።በ13ቱ ሳይቶች የታቀደው 63.26ኪ.ሜ በአረንጓዴ ለመሸፈን ሲሆን እስከአሁን 52 ሄክታር አረንጓዴ የለበሰ መሆኑን የከተማው ማዘጋጃ ባለሙያዎች አስረድተውናል።በዚሁ ኮሪደር ልማት 15 የህዝብ መፀዳጃ ቤት ለመስራት ታቅዷል። በየመስመሩ ላይ በዘመናዊ የተሰሩ መብራቶች አሉ።እንዲሁም 135 ካሜራዎች በከተማው ይገኛሉ።











ፎቶ 12፡- የኮሪደር ልማት

2.15. ሀይቆች

በቢሾፍቱ ከተማ 7 ሀይቆች ያሉ ሲሆን እነሱም፡-

1. ቢሾፍቱ ሀይቅ
2. ሆራ ሀዶ ሀይቅ/መገሪስ
3. ባቦጋያ ሀይቅ
4. ኩሪፍቱ ሀይቅ
5. አርሰዲ ሀይቅ
6. ጨለለቃ ሀይቅ
7. ኪሎሌ ሀይቅ ናቸው

በቢሾፍቱ ከተማ በአከባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ከትትልና ቁጥጥር እና የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት መኖሩ ለሀይቆቹ ደህንነት አስተዋጽኦ አድርጓል። እነዚህ ሀይቆችም ለከተማው ውበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው።

2.16. ችግኝ ጣቢያ

በቢሾፍቱ ከተማ 3 ችግኝ ጣቢያዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ ችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ ጨለለቃ ችግኝ ጣቢያን አንዱ ነው።የዚህ ችግኝ ጣቢያ ባለቤት መንግስት (የከተማው ማዘጋጃ) ሲሆን የችግኝ ጣቢያው ስፋት 2.5 ሄክታር ነው።በዚህ ችግኝ ጣቢያ ውስጥ በግሪን ሀውስ ውስጥ እና ውጭ ያሉ የተለያዩ ችግኞች አሉ።በዚህ 2016 ዓ.ም የተለያዩ ዝርያ የሆኑ 8.4 ሚሊዮን ችግኞች የተዘጋጁ ሲሆን 20% ለደን የሚሆኑ ችግኞች 30% ለምግብ የሚሆኑ ችግኞች እና 50% ለውበት የሚሆኑ ችግኞች ናቸው።ከነዚህ ውስጥ የሚበሉ አቡካዶ፣ዘይቱና፣ ፓፓያ፣ ማንጎ፣ ጥቂቶቹ ሲሆኑ ለውበት ከሚሆኑት ውስጥ ፊከስ፣ዱራታ፣አስተርናታ ውስኖቹ ናቸው። ለደን ደግሞ ጃካራንዳ፣ግራቪሊያ፣ዋነወዛ እና ብሳና ወዘተ የመሳሰሉ ዝርያዎች ናቸው።





ፎቶ 13፡- የጨለለቃ ችግኝ ጣቢያ

3. ክፍል ሦስት፡-

ማጠቃለያ

በቢሾፍቱ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ከመጀመሩ በፊት በከተማው የደረቅ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአቱ የተዝረከረከ ነበር።በዚህም የተነሳ የከተማው ነዋሪ ከአካባቢው መቆሸሽ የተነሳ ለጤንነት ችግር የተጋለጠ ነበር።በመሆኑም የከተማ አስተዳደሩ ይህንን ችግር በማየትና በመነጋገር የመፍትሄ እርምጃ ወስዶ ውጤት አስመዝግቧል። ከመነሻ አሁን እስካለበት (2017 ዓ.ም) ድረስ የተከናወኑ ሂደቶች እና የተገኙ ውጤቶች ለሌሎችም ትምህርት ይሆናሉ።

የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ የጀመረው በችግሩ አሳሳቢነት ዙሪያ በአመራርና ባለሙያዎች ደረጃ በመወያየት ወደ ቀጣዩ ሂደት በመራመድ ነው።ዕቅድ በማቀድ፣ ሕብረተሰቡን በማወያየት፣ ማህበራትን በማደራጀት፣ አመራሩንና ባለሙያዎችን በማጠናከር ወደ ስራ ገብቷል።ለሚመለከታቸው አካላትም ስለ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ግንዛቤ ፈጥሯል።በስራው ክንውን ላይ የቅርብ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የኃላፊነት ሚናውን ተወጥቷል።የተደራጁ ማህበራት ስራቸው በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ማሽን በመስጠት ድጋፍ አድርጓል።አካባቢያቸውን በተሻለ ጽዱ ላደረጉ መንደሮች ሞዴል መንደር ብሎ በመሰየምና በማበረታታት ለሌላው አርአያ እንዲሆኑ አድርጓል።

ከተማ አስተዳደሩ በዚህ ልክ በመስራቱ ከተማው በፊት ካለበት ችግር እና በቆሻሻ ብክለት ምክንያት ለበሽታ መጋለጥ ስጋት ከመሆን ተላቆ ዛሬ በሌሎችም ሊጎበኙ የሚችሉ ስፍራዎች ያለው ከተማ ወደ መሆን ደርሷል።በዕቅድ እየተመራ በቅንጅት በመሰራቱ የሚከተሉት ለውጦች/ውጤቶች ተገኝተዋል።

- በየቦታው ተዝረክርኮ ከተማውን ገጽታ ሲያበላሽ የነበረ ደረቅ ቆሻሻ አሁን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል
- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (Sanitary Land Fill) ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተሰርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል
- በፊት በየቦታው ተዝረክርኮ የበሽታ መንስኤ የነበረው ደረቅ ቆሻሻ አሁን ሀብት ሆኖ የገቢ ምንጭ ሆኗል
- ከደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ (ኮምፖስት) በማዘጋጀት ለጥቅም እንዲውል ተደርጓል
- በየቦታው በቆሻሻነት ያስቸግር የነበረ የፕላስቲክ በመልሶ ኡደት መጠቀም አገልግሎት መስጠት ችሏል
- ሕብረተሰቡ ቆሻሻ ገንዘብ መሆኑን እንዲያውቁት በተግባር አሳይቷል
- በማህበር የተደራጁ ዜጎች የስራ ዕድል እንዲያገኙ አድርጓል
- ቆሻሻን በማጽዳት፣የኮሪደር ልማቶችን በመስራት፣የውበትና መናፈሻ ስፍራዎችን በመፍጠር እንዲሁም በየመንደሩ ላሉ ነዋሪዎች ግንዛቤ በመፍጠር አካባቢያቸውን ጽዱና ውብ እንዲያደርጉ ስራ መስራቱ ለእይታ ከማማሩም አልፎ የአየር ንብረቱ ለጤና ምቹ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

“አካባቢያችንን ተንከባከበን ለጤና ተስማሚና ምቹ እናድርግ”